## የቅዱሳን አባቶች እርግማን ወይስ ምርቃን (አዳነ መኮነን)



1ኛ ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ
በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ
ከ ፲፱፻፵፬ ዓም - ፲፱፻፶፯ ዓም (1952-1965)

በቤተ ክህነት ሲያገለግሉ ከነበሩት ቅዱሳን አባቶችና እንዲሁም ለአንዲት ኢትዮጵያ ብለው ደማቸውን አፍስሰው አጥንታቸውን ከስክሰው አምስት ዓመት ሙሉ በዱር በገደሉ ተንከራትተው እነሱ ያቆዮአትን ሀገር ከሀዲዎችና ባንዳዎች ሲያፈርሷትና ሲከፋፍሏት ታይቷቸው እውነት ኢትዮጵያ የባለ እውነት ልጅ ይውጣብሽ ብለው የተናገሩ ብዙ ናቸው። ስለእናት ሀገር ኢትዮጵያ ደህንነትና አንድነት በየዘመኑ እንደየሁኔታውና እንደየ ድርሻቸው ራሳቸውን መሥዋዕት ያደረጉ ልጆችዋ እልፍ አእላፋት ሲሆኑ አንዳንዶቹንም በተቻለ መጠን በዚሁ መጽሐፍ አለፍ አለፍ ብለን ሳናወሳቸው አልቀረንም። ከነዚህም አንዱ የሁኑት የዚህ ምእራፍ እንግዳችን አቡን ፊሊጶስ ይሆናሉ።

በአንድ ወቅት በሻእቢያና በመንግሥት በኩል እርቀ ሰላም ይሁን በማለት የሰላም ቡድን ተቋቋመ። የቡድኑ መሪ አቡነ ፊሊጶስ የሚባሉ የሐማሴን ተወላጅ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን ጳጳስ ሲሆኑ ይህውም የኤርትራን ባላባቶችና የአገር ሽማግሌዎችን ለእርቀ ሰላም ለማነጋገር የሄዱ ሁሉም የኤርትራ ሕዝብ ቀና አመለካከትና በጐ መንፈስ ያሳዩበት ወቅት ነበር። የነህን ቅዱስ አባት ማለትም የብፁዕ አቡነ ፊልጶስን የሰሩትን ጥሩ ምግባርና የተናገሩትን ወይም በዚያን ጊዜ ወደፊት የሚሆነው የኢትዮጵያ እጣ ፈንታ ምን እንደሚሆን አስቀድሞ ታይቶአቸው አዝነው የተናገሩት ነገር ደረሰ፤ከሌላ መጽሐፍ የአገኘሁትን እንደ መንደርደርያ አድርጌ ለአቅርብ። የእነህን አባትና ስለቡዱኑ ድካም ዘነበ ፈለቀ ነበር በሚለው በገጽ (164-166) መጽሀፉ እንዲህ ሲል ይተርከዋል።

“....ጓደኛዬ አምስት ቀናት ያህል አዲስ አበባ ቆይቶ ወደ አሥመራ ሲመለስ እርሱ በሌለበት የተፈጸሙ አበይት ተግባራትን ባጭር ባጭሩ ገለጽኩለት። በተለይ በሁለተኛ ክፍለ ጦር መምሪያ ውስጥ ለሁለታኛ ጊዜ ተቆስቁሶ እንደገና ለተዳፈነው የበታች ሹሞች አመጽ አብራራሁለት እርሱም ጉዳዩን ሻለቃ መንግሥቱ ገልጸውለት እንደነበር ነገረኝ። እንዳጋጣሚ ሆኖ የዚያውኑ እለት ምሽት የእርቅ አፈላላጊው ቡድን አባላት ከአቁርዳት ተመለሰው ስለነበር ወዳረፉበት ሆቴል ሂደን ስናጫውታቸው አመሸን። ሽማግሌዎቹም ድካም ቢጫናቸውም ተልእኮአቸውን ከግቡ ለማድረስ የጠነከረ ጉጉት ይታይባቸው ነበር። የከፍለ ሀገሩን ምዕራባዊ ቆላ አውራጃ ከተሞችን በሙሉ አዳርሰው የሀገር ሽማግሌዎችን አነጋግረው ሁሉም ሰላም ፈላጊዎች መሆናቸውን አረጋግጠውላቸዋል። አሁን የቀረን የሻእቢያ መሪዎችን አግኝተን ማነጋገር ነው የቀረን አሉ አቡነ ፊሊጶስ። እነርሱ ካሉበት ቦታ ለመድረስ አይደክማችሁንም?...ብሎ ጓደኛዬ ጠየቃቸው ፤በዳዴም ቢሆን ሂደን የሚሉነን መስማት አለብን በማለት አቡኑ መልስ ሲሰጡ የመንፈስ ጥንካሪያቸውን አደነቅሁ። የሰላም ናፍቆትና የወገንና የሀገር ፍቅር ስሜት እድሚያቸው ከሚፈቅድላቸው በላይ ለመሥዋዕትነት እንዳነሳሳቸው ሳስተውል እራሴን እንድፈትሽ ተገደድኩ። እኔም ሰላም እፈልጋለሁ የወገንና የሀገር ፍቅር ስሜት በውስጤ አለ ለዚህ

ማንኛውንም መስዋእት ለመክፈል ዝገጁ ነኝ እንደ አቡነ ፊሊጶስ ጳጳስ ሁኜ ከሁሉም በላይ መቃብሬ የተማሰ የመግነዜ ልጥ የተራሰ ሽማግሌ ሁኜ ግን ያን ያህል መስዋእትነት ለመክፈል የምነሳ አይመስለኝም። ይልቁንም አያቶቻችን አባቶቻችን እኛም ይችን ሀገር ይን ያህል እንድናፈቅራት ያደረገን ምንዋ ይሆን? የሚል ጥያቄ መጣብኝ ይህም ጥያቄ እድሜ ልኬን በውስጤ የሚኖር ይመስለኛል። ከጢቂት ቀናት የመረጃ ጥረት በኋላ አቶ ኢሳይያስ አፈወርቂ ከምጽዋ ሰሜን በኩል ቀይ ባህር ጠርዝ ላይ ሼእብ በምትባል ከተማ ውስጥ እንደሚገኙ ራሻዒዳ ከሚባሉ ጎሳዎች በኩል በተገኘ መረጃ ተረጋግጠ። ከዚያም ከሻለቃ መንግስቱ ጋራ በስልክ በተደረገ ምክክር (ጓደኛዬ አዲስ አበባ በቆየበት ጊዜ እንደተመካከርነበትና ይኸኛው የማጠናከሪያ ምክክር እንደሆነ እገምታለሁ) በክፍለ ሀገሩ አስተዳደር ስም ለአቶ ኢሳይያስ አፈወርቂ የሚሰጥ ደብዳቤ ተሰናዳ። የደብዳቤውም ይዘት ሰላምታና ቡዱኑም እርቅና ሰላም አፈላላጊ መሆኑን በጎ ምላሽ ይዞ እንደሚመለስ የክፍለ ሀገሩ አስተዳደር ያለውን ተስፋ በዚሁ ጅምር መንግሥትና ሻእቢያ ለሰላማዊ ድርድር እንደሚበቁ የሚገልጽ መልካም ምኞትና ፍላጎትን ያካተተ ነበር። ከዚህ በኋላ ሁላችንም ወደምጽዋ ወረድን በማግስቱ የቡዱኑ አባላት በመኪና ወደ ሼእብ ተጓዙ። የሼእብ ወረዳ በረሃ በመሆኑ ካምሲን የሚባል አውሎ ነፋስ ይመታዋል፤ ሽማግሌውቹ የፀሐዩን ሐሩርና ከምሲኑን ተቋቁመው ከስፍራው ደርሰው ከሦስት ቀናት በኋላ ይመስለኛል ተመለሰው መጡ። ምጽዋ ቤተ መንግሥት ተቀብለን እንዲያርፉ አደረግን በጣም ደክሟቸው ነበር። አቡኑ ግን "እስኪ ወደባሕሩ ዳርቻ ውሰዱኝ?"አሉን፤ ለመርከብ መሳፈሪያ የሚያገለግል ከቤተ መንግሥቱ ምሥራቅ በኩል ወደሚገኝ አንስተኛ ባሕረገብ (ደረጃና የብረት በረንዳ ወደ አለው) ወሰድናቸው። የሰገነቱን ብረት በእጃቸው አጥብቀው ይዘው ተደገፉትና ቀይ ባሕርን ስክክ ብለው እየተመለከቱ ለራሳቸው በሚመስል አነጋገር ሰደበኝ እኮ ይህ ባለጌ ሰደበኝ (አቶ ኢሳይያስ አፈወርቂን) ማለታቸው ነበር፤ የአማራው ጳጳስ አቡነ ጴጥሮስ ከኢጣልያን ጋር ተዋግቶ በጀግንነት ሞተ አንተ ግን ባንዳ ሁነህ በእርቀ ስም እጃችሁን ስጡ ልትለን መጣህ?. አለኝ ፍረዳ አንተ ባሕር የኢትዮጵያ ልጆች ለአንተ ሲሉ አንገታቸውን ለሰይፍ አለሰጡምን? ደማቸውን ከውሃህ ጋር አልቀላቀሉምን? እነ አሉላ እዚህ ድረስ የመጡት ምን ሊሰሩ ኑሯል አሁን አንተ የኢትዮጵያ አይደለህም? እያሉ አለቀሱ አኳኋናቸውም እኛን አስለቀሰን።
እባክዎ አይበሳጩ እርሱ እኮ ሽፍታ ነው አላቸው ጋደኛዬ፤ በዝምታ አለቀሱ በጉንጫቸው ላይ ከሚኳለለው እንባቸውን በጣታቸው ጠረግ አድርገው ወደ ባሕሩ ፊነጠቁና በገፍ ተንፍሰው ሲያበቁ ውሰዱኝ ከእንግዲህ ልረፍ አምላኬ የኢትዮጵያን መጥፎ ነገር ሳያሳየኝ በገደለኝ ብለው በለሆሳስ ተናገሩ። ጓደኛዬ በመደገፍ አኳኋን እጃቸውን ያዝ አድርጎ ከሚያርፉበት ክፍል አድርስዋቸው ተመለሰ ትክዝ ብለን እዚያው መርከብ መሳፈሪያ ሰገነቱ ላይ በዝምታ እንደቆምን የእኒህን ሰው ነግግር እናስቀረው አልኩት ጓደኛዬን፤ እርሱም በሀሳቤ ተስማምቶ እርሳቸው ከእንቅልፋቸው እስከሚነቁ ድረስ መቅረጸ-ድምጽ አሰናድተን ጠበቅናቸው። ከምሽቱ 12 ሰዓት ገደማ ከሚኙታቸው ተነስተው በቤተ መንግሥቱ በረንዳ ላይ ሲነሸራሽሩ አገኘናቸው። ከዚያም ስለእርቀ ሰላሙ ጥረታቸውና ስለኢትዮጵያ አንድነት ያላቸውን አስተያየት በመቅረጸ-ድምጽ ልናስቀር እንዳሰብን ገለጽነላቸው። እርሳቸውም በሃሳባችን ስለተስማሙ አንዳንድ አነሳሽና አሰተዋሽ ጥየቄዎችን እየሰነዘርኩላቸው መናገራቸውን ቀጠሉ። በዚያን ወቅት የአቡነ ፊሊጶስ ድምጻቸውን ብቻ ሳይሆን ፎቶ ግራፍ ማንሻ ብይዝ ኑሮ ምስላቸውንም ማስቀረት ነበረብኝ፤ ይህን ባለመድረጌና ለማያውቋቸው ማሳወቅ ባለመቻሌ እስከ አሁንም ድረስ ይቆጨኛል። እኔማ ምንጊዜም እንዳስታወስኳቸው እኖራለሁ፤ ያ በጥቁር ጳጳስ ልብስ የተጀቦነው ጀርጋዳ ቁመናቸው ብስል ቀይ መልካቸው ፍጹም ርጋታ የተላበሰው ገጽታቸውና ከሁሉም በላይ ቀይ ባሕር ጠርዝ ላይ ቆመው ያነቡትና ወደ ባሕሩ የፈነጠቁት እንባቸው ከልቤ አይጠፋም። ለአንድ ሰዓት ያህል ከአነጋገርናቸው በኋላ አበቃን በማግስቱም ወደ አስመራ ተመለስን። በዚሁ የእርቅ አፈላላጊው ቡድን ተልእኮ አብቅቶ ያለውጤት ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ"።

ውድ አንባቢዎች እኔም የማያውቃቸው ሕዝብ እንዲያውቃቸው ብዬ ፎቶ አቸውንና የሕይወት ታሪካቸውን በመጠኑ አስቀምጬዋለሁ። እግዚአብሔር የነገሩትን አይረሳም የለመኑትን አይነሳም እና እኒህ የበቁ አባት እግዚአብሔር ፀሎታቸውን ሰምቶ ከላይ እንደተናገሩት የኢትዮጵያን መጥፎ ነገር ሳያሳያቸዉ አርፈዋል። በፁዕ አቡነ ፊሊጽስ ዘኢየሩሳሌም (በ1888 ዓ/ም) በሀማሴን አውራጃ ተወለዱ በተወለዱበት ደብር ተማሩ 1901 ባድዋ ሀዲ አቡን ከግበፃዊዉ አቡነ ጴጥሮስ ዲቁና ተቀበሉ ባቡነ

እንድርያስ ገዳም መነኮሱ በደብር ዐባይ ገዳም ባዲስ አበባ ተማሩ ከበፁዕ አቡነ ማቴዎስ ግበፃዊ ቅስና ተቀበሉ በታዕካ ነገሥት በአታ ለማርያም (ከ1925-1928) ሊቀ ሊቃውንት ሁነው ተሾሙ (1943-1957) በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ሊቀ ጳጳስ ሆነዉ አገልግለዋል በፁዕነታቸው በርካታ መጽሓፍትን ጽፈዋል (በህዳር 16 ቀን 1974 በ87) ዓመት ዕድሜአቸው አርፈዋል። እንግዲህ እኒህን ደግ አባት በኢትዮጵያዊነታቸው አምነው የኢትዮጵያን ችግር ሳያዩ ማረፋቸውን አስተውሉት። የህይወት ታሪካቸውን ዝክረ አበው መጽሔት ነው ያገኘሁት።

በአሁኑ ሰዓት አንዳንድ ኤርትራዊ የኤርትራ መሞት በዚያን ጊዜ ያልተገለጠላቸው አሁን ከሞተች በኋላ ተገልጦላቸው ኤርትራ ሞተች እያሉ ይጽፋሉ ይናገራሉ። የመሞቷ ምልክት እማ ኤርትራውያን በዓለም ተሰደው ሀገር የላቸውምና በገቡበት ሀገር ሁሉ ጥገኝነት እንዲያገኙ ብሎ የተባበሩ መንግሥታት አሳወቀላቸው። እርግጥ ስደት ሁሉም ይሰደዳል ሀገር ግን የለውም አልተባለም። ይህ ታዲያ እርግማን ወይስ ምርቃን ሆኖ ደረሰ እኒህ አባት የተናገሩት። እንዲሁም አቶ ኢሳይያስ አፈወርቅ በዚያን ጊዜ የኒህን ቅዱስ አባት ምክር አልቀበልም ብለው የተሳደቡት፤ ከነጻነት በኋላ እንደ ሲጋፖርና እንደ ታይዋን ኤርትራ ትሆናለች ያሉት ህልማቸው ሳይሳካ ቀርቶ ሲረዱት ከሃያ አራት ዓመት በዋላ የኢትዮጵያንና የኤርትራን ሕዝብ የፈለገ መንግሥት ቢመጣ ሊቀይረው አይችልም ሲሉ ተናገሩ። በአንዲት ሀገር ሁለት መንግሥት ተቀመጡ እንጂ እሳቸው ተናገሩ አልተናገሩ ሕዝቡ ጥንትም ሆነ ዛሬ ወደፊትም ቢሆን አብሮነቱንና አንድነቱን ማንም የሚቀይረው የለም። ደግሞም ስህተታቸውን ለማመንም ላለማመንም ዳርዳር ብለዋል፤ይህውም ለሚመጣው እንጂ "ለአለፈ ክረምት ቤት አይሰራም" እንደሚሉት እሳቸውም ለሚመጣው ጥሩ መሥራት እንጂ ለአለፈው ጥፋት ተጠያቂ መሆን አያስፈልግም ሲሉ ተደምጠዋል። እርግጥ ያለፈው ትምህርት ከሆናቸው ጥሩ ነው። አሁንም ለወደስተፊቱ ልባቸውን የቀና ነገር እንዲያስብ እግዚአብሔር ይርዳቸው ሰው ቀጥፋቱ ከተመለሰ እንኳን እግዚአብሔር ሰውም ይቅር ይላል።

ውድ ወገኖቼ እኒህን አባት እንደ ምሳሌ አድርጌ አቀረብኩ እንጂ እንዲህ ያለ ሥራ ሰርተው ያለፉ ብዙ ናቸው። የጥንት አባቶች ጸሎታቸውና ጉልበታቸውን ለቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ለአገር ጭምር እንደሰሩና ሕይወታቸውን አሳልፈው ሰጥተው እንደ ተሰዉ እናውቃለን። የአሁኖቹ ግን ለሀገር ቀርቶ ለተሾሙባት ቤተ ክርስቲያን ያልታደጉና ያልሰሩ፤ ለሕዝበ ክርስቲያን ከተኩላና ከነጣቂ ቀበሮ መጠበቅ የቃአታቸውና የተሳናቸው መሆኑን በግልጽ እያሳዩን ነው። የተወሰኑትም አልፈው ሄዱ የቀሩትም በዚያው እንደቀጠሉ ይታያሉ፤እንዲያውም ከነፍሳቸው ይልቅ የሥጋቸው በልጦባቸው በፖለቲካው ውስጥ እጃቸውን አስገብተው ቤተ ክርስቲያንን ሲበጠብጧትና ሕዝበ ክርስቲያኑን በቡድን በቡድን ከፋፍለው ሲያፋጇት ይታያሉ። ወዮልህ አንተ ቁራ አሞራ ራስ ነጭ ገላህ ጥቁር የሆንከው እያለ የሚናገረውን፤ፍካሬ ኢየሱስ የሚለውን ዘንግተው። የማያልፈውን በሚያልፍ ቀይረው ለዘላለም የሚሆነውን የሰማዩን መኖሪያ ቤታቸውን ሳይሆን ድንገት ተጠርተው ጥለውት የሄዱትን የምድሩን ቤታቸውን የወርቅ ምንጣፍ አንጥፈው ሰውነታቸውን ወርቅ በወርቅ አድርገው ሲኃባለሉ ሳለ ንስሐ ሳይገቡ ከፈጣሪያቸው ጋር ሳይታረቁ ያ የማይምረው መላእከ ሞት መጥቶ እንደ ወሰዳቸው ታውቃላችሁ። ጥለውት የሚሄዱትን የጊዜያዊውን የምድሩን ቤታቸውን አስጊጠው፤ አሳምረው ሲሠሩና ሥጋቸውን ሲያደልቡ፤ ነገ ከነገ ወዲያ ምን እንደሚመጣና ምን እንደሚፈጠር ሳያውቁ አሁንም የቀሩትን እያየናቸው ነው። አሞሌ ጨው ለራስህ ስትል ጣም ካለበለዚያ ግን ድንጋይ ነው ብለው ይጥሉሃል አበው እንደሚሉት፤ካህናትም ለእግዚአብሔር፤ለቤተ ክርስቲያንና ለሕዝበ ክርስቲያን ጣፋጭ ሁናችሁ ቅረቡ ካለበለዚያ ግን እናንተንም ድንጋይ ናችሁ ብሎ ፍጣሪ እሳቱ ከማይጠፋበት ትሉ ከማያቀላፋበት ወደ ሲኦል ወርውሮ እንዳይጥላችሁ፤ ምክንያቱም መውጊያው ለአንተ ይብስብሃል የሚለውን የእግዚአብሔርን ቃል ከልብ አንብባችሁ አልተረዳችሁትምና። መስቀል የምትጨብጡት ዳዊት የምታነግቡት ሁሉም ነገር ለታይታ ነው፤ ጳጳስ ሳትሆኑ ጳጳስ መሆን፤መነኩሴ ሳትሆኑ መነኩሴ

መሆን፤ ዲያቆን ሳትሆኑ ዲያቆን መሆን፤ መምህር ሳትሆኑ መምህር መሆን፤ ዘማሪ ሳትሆኑ ዘማሪ መሆንን አቁሙ፤ ይህን ስል ግን ሁሉንም ቤተክርስቲያንን የሚያገለግሉትን እውነተኞቹን አይጨምርም፤ አይመለከትም አስመሳዮችን በፖለቲካ በዘር በጎሳ የተጠመዱትንና የተበከሉትን ነው። በሀገርም፤ በውጭም የምትገኙት ሕዝበ ክርስቲያን ወገኖቼ በሙሉ፤ ይህን በቤተ ክርስቲያን የገባውን ሰይጣን የአሁኖቹ ካህናት ተዋግተው ሊያስወጡት አልቻሉም ፤የጥንት አባቶቻችን በተፈጥሮም ይሁን በሰው ሰራሽ መከራና ስቃይ ሲደርስባቸው በጎጥና በመንደር እየተሰባሰቡ ምህላና እግዚኦታ ለአምላክ ያሰሙ ነበር፤ እግዚአብሔርም በንጹህ ህሊና በቅን ልቦና ሆነው ወደ እርሱ እጃቸውን ዘርግተው የለመኑትንና የጠየቁትን ወዲያው ይሰጣቸው፤ ወይም ይሰማቸው ነበር። እናንተም አሁን በቅን ልቦና በንጹህ ህሊና ሁናችሁ በአንድ ተሰባስባችሁ እንደዚያ አድርጋችሁ ብትለምኑት ጸሎታችሁንና ልመናችሁን ሰምቶ መልሱን ወዲያው ይሰጣችኋል። እግዚአብሔር ሀገራችን ኢትዮጵያንና ሕዝቧን እንዲሁም ተዋህዶ ቤተክርስቲያናችንን ይጠብቅልን አሜን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!!!

መጋቢት ፪ ቀን ፳፻፯፤ ዓ/ም (11/03/2015)